## <u>መመሪያ ቁጥር 2/2012</u>

## <u>የኮቪድ-19 ሥርጭትን ለመከላከል፤ ለመቆጣጠር እና የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ የወጣውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እና አዋጁን ለማስፈጸም የወጣውን ደንብ ለማስፈጸም በሚኒስትሮች ኮሚቴ የወጣ መመሪያ</u>

የሚኒስትሮች ኮሚቴ የኮቪድ-19 ሥርጭትን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ የታወጀውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር 3/2012 ለማስፈፀም በወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 466/2012 አንቀፅ 7 መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፣

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. <u>**አጭር ርእስ**</u>

   ይህ መመሪያ " **የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እና አዋጁን ለማስፈጸም የወጣውን ደንብ ማስፈፀሚያ የሚኒስትሮች ኮሚቴ መመሪያ ቁጥር 2/2012**" ተብሎ ሊጠራ ይችላል

2. <u>**ትርጓሜ**</u>

   በዚህ መመሪያ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

1/ ደንብ ማለት የኮቪድ-19 ስርጭትን ለመከላከል፣ለመቆጣጠር እና የሚያስከትለዉን ጉዳት ለመቀነስ የወጣዉ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር 3/2012ን ለማስፈፀም የወጣዉ ደንብ ቁጥር 466/2012 ነዉ፤

2/ የሚኒስትሮች ኮሚቴ ማለት በደንብ ቁጥር 466/2012 የተቋቋመዉ ኮሚቴ ነዉ፤

3/ አሰሪ ማለት በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 መሰረት ሰራተኞችን የሚያስተዳደር ግለሰብ፣ድርጅት፣ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅትና ሌላ በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 የተመለከተ ተቋም ነው፣

4/ ሰራተኛ ማለት በግለሰብ፣ በድርጅት፣ በመንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ሌሎች ተቋማት ተቀጥሮ የሚሰራና በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 መሰረት የሚተዳደር ሰራተኛ ነው፣፤

5/ በአዋጁ እና በደንቡ ትርጉም የተሰጣቸዉ ቃላትና ሐረጎች ለዚህ መመሪያም ተፈፃሚ ይሆናሉ፤

3. <u>**የተፈፃሚነት ወሰን**</u>

   ይህ መመሪያ በመላ ሀገሪቱ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁና ደንቦች ተፈፃሚ በሚሆኑባቸው ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል:

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Federal Attorney General

Scanned by CamScanner

## ክፍል ሁለት

## የሚኒስትሮች ኮሚቴ አሰራር፣ የኮሚቴው አባላት፣ ስለንዑሳን ኮሚቴዎችና በክልሎች ስለሚቋቋሙ ኮሚቴዎች፤

**4. ስለኮሚቴው ሰብሳቢና ተጠሪነት**

የሚኒስትሮች ኮሚቴ ተጠሪነት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ሲሆን የእለት ከእለት ስራውን በተመለከተ በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሰብሳቢነት ይመራል፣

**5. የኮሚቴው አባላት**

1/ የሚኒስትሮች ኮሚቴ አባላት የሚከተሉት ናቸው:-

ሀ. የሰላም ሚኒስቴር ሚኒስትር፣

ለ. የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ፣

ሐ. የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ሚኒስትር፣

መ. የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትር፣

ሠ. የመከላከያ ሚኒስቴር ሚኒስትር:

2/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው ቢኖርም ኮሚቴው የህግ አስከባሪ አካላትና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን አካላት ያሳትፋል፣ተልእኮ ይሰጣል፣ የተሰራውን ስራ ይገመግማል ፣ አቅጣጫ ይሰጣል፣

3/ ለዚህ አንቀፅ አላማ **"የህግ አስከባሪ አካላት"** ማለት መከላከያ፣ የፌዴራልና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፖሊስ ኮሚሽኖች፣ የብሄራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት፣ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ፣ የአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ማእከል ናቸው፡፡

**6. የኮሚቴው የአሰራር ስርአት**

1/ የሰላም ሚኒስቴር የሚኒስትሮች ኮሚቴ ሴክሬታሪያት በመሆን ያገለግላል፣

2/ ኮሚቴው በየእለቱ የመረጃ ልውውጥ የሚያደርግ ሲሆን በየሶስት ቀኑ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፣

3/ አስቸኳይ ስብሰባ በማናቸውም ጊዜ በሰብሳቢው ሊጠራ ይችላል፤

4/ የስብሰባው ሁኔታ በአካል በመገኘት ወይም በኦንላይን አማካኝነት ሊደረግ ይችላል፤

5/ በኮሚቴው ስብሰባ ከግማሽ በላይ አባላት ከተገኙ ምልዐተ-ጉባኤ ይሆናል፤

6/ የኮሚቴው የውሳኔ አሰጣጥ ስርአት በድምፅ ብልጫ ይሆናል፣

7/ የድምፅ አሰጣጡ ስርዓት እጅ በማውጣት ይሆናል፤

8/ የአባላት ድምፅ እኩል ሲከፈል ሰብሳቢው ያለበት የኮሚቴው ውሳኔ ይሆናል፤

9/ ኮሚቴው ዝርዝር የአሰራር ስርአቱንና ክልላዊ ኮሚቴዎች ጋር የሚኖረውን ግንኙነት በተመለከተ ዝርዝር እቅድ ያወጣል፡፡

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ The Federal Democratic Republic of Ethiopia Federal Attorney General

Scanned by CamScanner

7. **ንዑሳን ኮሚቴዎች**

የሚከተሉት ንዑሳን ኮሚቴዎች በዚህ መመሪያ ተቋቁመዋል

1/ የኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ንዑስ ኮሚቴ

2/ የህግ ጉዳዮች ንዑስ ኮሚቴ

3/ የዲፕሎማሲ ጉዳዮች ንዑስ ኮሚቴ

4/ (የህግ አስከባሪ) የፀጥታ ጉዳዮች ንዑስ ኮሚቴ

5/ የቴክኖሎጂ ጉዳዮች ንዑስ ኮሚቴ

8. **የኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ንዑስ ኮሚቴ ተጠሪነት፤ተግባርና ሃላፊነት**

1/ የኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ንዑስ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለሚኒስትሮች ኮሚቴ ነው፣

2/ የኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ንዑስ ኮሚቴ በሰላም ሚኒስቴር ሚኒስትር ይመራል፤

3/ የኮሚዩኒኬሽን ንዑስ ኮሚቴ ተግባርና ሃላፊነት :-

የኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ንዑስ ኮሚቴ የሚከተለው ተግባርና ሃላፊነት ይኖረዋል፤-

ሀ. የኮቪድ-19 ወረርሽኝን ለመከላከል፣ለመቆጣጠርና የሚያደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ የወጣውን አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ አፈፃፀምን በተመለከተ የሚሰሩ የኮሚዩኒኬሽን ስራዎችን በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፤

ለ. የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ፣ደንብና መመሪያ አፈፃፀምና አተገባበርን አስመልከቶ መረጃ፣ማስረጃ ና ሪፖርት ያጠናቅራል፣ ያሰባስባል፣ ያሰራጫል፤

ሐ. የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ አፈፃፀምን አስመልክቶ ለሚነሱ ጥያቄች ማብራሪያ ይሰጣል፤

4/ የኮሚዩኒኬሽን ንዑስ ኮሚቴ በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ከሚቋቋሙ ተመሳሳይ ንዑሳን ኮሚቴዎች ጋር በጋራ፣ በቅንጅትና በትብብር ይሰራል፣

9. **የህግ ጉዳዮች ንዑስ ኮሚቴ ተጠሪነት ፣ ተግባርና ሃላፊነት**

1/ የህግ ጉዳዮች ንዑስ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለሚኒስትሮች ኮሚቴ ነው፣

2/ የህግ ጉዳዮች ንዑስ ኮሚቴ በፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ሰብሳቢነት ይመራል፤

3/ የህግ ጉዳዮች ንዑስ ኮሚቴ ተግባርና ሃላፊነት:-

የህግ ጉዳዮች ንዑስ ኮሚቴ የሚከተለው ተግባርና ሃላፊነት ይኖረዋል፤-

ሀ. የኮቪድ-19 ወረርሽንን ለመከላከል፣ለመቆጣጠርና የሚያደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ የወጣ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎች ላይ የህግ ትንታኔና ማብራሪያ ይሰጣል፤

ለ. አስቸኳይ ጊዜ አዋጁን በተመለከተ የሚረቀቁ ደንብና መመሪያዎች ካሉ የመለየት፣ የማርቀቅና ለሚመለከተው አካል የማቅረብ ሀላፊነት አለበት፡፡

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ The Federal Democratic Republic of Ethiopia Federal Attorney General

Scanned by CamScanner

4/ የህግ ጉዳዮች ንዑስ ኮሚቴ በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ከሚቋቋሙ ተመሳሳይ ንዑሳን ኮሚቴዎች ጋር በጋራ፣ በቅንጅትና በትብብር ይሰራል::

**10. የዲፕሎማሲ ጉዳዮች ንዑስ ኮሚቴ ተጠሪነት ፣ ተግባርና ሃላፊነት**

1/ የዲፕሎማሲ ጉዳዮች ንዑስ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለሚኒስትሮች ኮሚቴ ነው፣

2/ የዲፕሎማሲ ጉዳዮች ንዑስ ኮሚቴ በውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትር ሰብሳቢነት ይመራል፤

3/ የዲፕሎማሲ ጉዳዮች ንዑስ ኮሚቴ ተግባርና ሃላፊነት:-

የዲፕሎማሲ ጉዳዮች ንዑስ ኮሚቴ የሚከተለው ተግባርና ሃላፊነት ይኖረዋል፤-

ሀ. የኮቪድ-19 ወረርሽንን ለመከላከል፣ለመቆጣጠርና የሚያደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ ከውጪ ሀገራት ጋር በተያያዘ የሚሰሩ ስራዎችን በበላይነት ይመራል፤

ለ. የኮቪድ-19 መከሰት ከሌሎች ሀገራት ጋር በሚኖረን ግንኙነት ላይ የሚያሳድረውን ተፅእኖ ወይም የሚያመጣውን ለውጥ ያጠናል፣ ይተነትናል ለሚኒስትሮች ኮሚቴ ያቀርባል፤

ሐ. በሌሎች ሀገሮች የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ከኮቪድ-19 ጋር በተያያዘ የሚደርስባቸውን ተፅእኖ፣ ጫና እና ሌሎች መሰል ጉዳዮች በቅርበት ይከታተላል የውሳኔ ሀሳብ ለሚኒስትሮች ኮሚቴ ያቀርባል፤

መ. ለዲፕሎማቶች ኮቪድ-19 በሀገራችን ስለሚገኝበት ሁኔታና መሰል ጉዳዮች መረጃ ይሰጣል፤

ሠ. ሌሎች ከኮቪድ-19 ጋር በተያያዘ ከዲፕሎማቶችና ከውጪ ሀገራት ጋር የሚሰሩ ስራዎችና አለማቀፍ ግንኙነቶችን አስመልክቶ አስፈላጊውን ሁሉ ያደርጋል፣

**11. (የህግ አስከባሪ) የፀጥታ ጉዳዮች ንዑስ ኮሚቴ ተጠሪነት ፣ ተግባርና ሃላፊነት**

1/ የፀጥታ ጉዳዮች ንዑስ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለሚኒስትሮች ኮሚቴ ነው፣

2/ የፀጥታ ጉዳዮች ንዑስ ኮሚቴ በመከላከያ ኢታማዦርሹም ሰብሳቢነት ይመራል፤

3/ የፀጥታ ጉዳዮች ንዑስ ኮሚቴ ተግባርና ሃላፊነት :-

የፀጥታ ጉዳዮች ንዑስ ኮሚቴ የሚከተለው ተግባርና ሃላፊነት ይኖረዋል፤-

ሀ. የኮቪድ-19 ወረርሽንን ለመከላከል፣ለመቆጣጠርና የሚያደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ የወጡ ህጎች ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፣ አፈፃፀማቸውን በበላይነት ይመራል፤

ለ. ሁሉም የፀጥታ አካላት ከኮቪድ-19 ጋር በተያያዘ የሚሰሩ የፀጥታ ስራዎችን በበቂ ሁኔታ ለማከናወን በቂ ዝግጅት ማድረጋቸውን ይገመግማል፣ አስፈላጊ አቅጣጫ ይሰጣል፣

ሐ. በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የሚገኙ የፀጥታ አካላት ኮቪድ-19ን ለመከላከከልና ለመቆጣጠር እንዲያስችሉ የወጡ ህጎችን ለማስፈፀም በቂ ዝግጅት ማድረጋቸውን ይገመግማል፣ አቅጣጫ ይሰጣል፣

መ. የህጎቹን አፈፃጸም ይገመግማል ክፍተቶች በሚፈጠሩ ጊዜ አስፈላጊውን አቅጣጫ ይሰጣል፣

ሠ. በአስቸኳይ ጊዜ ወቅት አጠቃላይ የሰላምና ፀጥታውን ሁኔታ በበላይነት ይመራል፣ ይገመግማል፣ አቅጣጫ ይሰጣል::

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ The Federal Democratic Republic of Ethiopia Federal Attorney General

Scanned by CamScanner

4/ የፀጥታ ጉዳዮች ንዑስ ኮሚቴ በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ከሚቋቋሙ ተመሳሳይ ንዑሳን ኮሚቴዎች ጋር በጋራ፣ በቅንጅትና በትብብር ይሰራል:

**12. የቴክኖሎጂ ጉዳዮች ንዑስ ኮሚቴ ተጠሪነት ፣ ተግባርና ሃላፊነት**

1/ የቴክኖሎጂ ጉዳዮች ንዑስ ኮሚቴ ተጠሪነት ለሚኒስትሮች ኮሚቴ ነው፣

2/ የቴክኖሎጂ ጉዳዮች ንዑስ ኮሚቴ በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ይመራል፣

3/ የቴክኖሎጂ ጉዳዮች ንዑስ ኮሚቴ ተግባርና ሃላፊነት

የቴክኖሎጂ ጉዳዮች ንዑስ ኮሚቴ የሚከተለው ተግባርና ሃላፊነት ይኖረዋል፡-

ሀ)ከአስቸካይ ጊዜ አዋጁ ጋር ተያይዞ የኮቪድ19 ወረርሽኝን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠርና የሚያደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ የሚደረጉ ጥረቶችን የሚያግዙ ቴክኖሎጂያዊ መፍትሄዎችን ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

ለ)የመረጃ ልውውጥ እና ሌሎችም ተግባራትን ቀልጣፋ በሆነ መልኩ ለማከናወን የሚያስችሉ የአሰራር ስርዓቶችን ያቀርባል፡፡

**13. በክልሎች የሚቋቋሙ ኮሚቴዎችና አባላት**

1/ በሁሉም ክልሎች ክልላዊ ኮሚቴና በተዋረድ ባሉ አደረጃጀቶች ተመሳሳይ ኮሚቴዎች ይቋቋማሉ፣

2/ ክልላዊ ኮሚቴው በክልሉ ፕሬዚዳንት የሚመራ ሲሆን በዞን፣በወረዳና በቀበሌ የሚደራጁ ሌሎች ኮሚቴዎችም ዞኑን፣ ወረዳውን ወይም ቀበሌውን በሚያስተዳደረው ከፍተኛ አመራር መመራት ይኖርባቸዋል፣

3/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 የተመለከቱት ኮሚቴዎች በየአደረጃጀቱ ያሉት በአዋጁ የተመለከቱትን የህግ አስከባሪ አካላትና ሌሎች ቫይረሱን ለመከላከልና ለመቆጣጠር እንዲሁም የሚያደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ በሚደረገው ጥረት በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ አስተዋፅኦ ሊያደርግ የሚችል ተቋም አመራር በአባልነት እንዲይዙ ይደረጋል፡፡

**14. የክልላዊ ኮሚቴው ተግባርና ሃላፊነት ፣**

ኮሚቴው የሚከተሉት ተግባርና ሃላፊነት አሉት፡-

1/ የኮቪድ-19 ሥርጭትን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ በክልሉ ወይም በከተማ አስተዳደሩ የሚሰራውን ስራ በበላይነት ይመራል ፣ ያስተባብራል፤

Scanned by CamScanner

2/ የቫይረሱን ስርጭት በተመለከተ ከፌዴራል የሚኒስትሮች ኮሚቴ የሚሰጠውን አቅጣጫ ይቀበላል፣ ያስፈፅማል ፣ ሪፖርት ያደርጋል፣ አስፈላጊውን መረጃና ማስረጃ ይሰበስባል፣ ይተነትናል፤ በትንተናው ላይ ተመስርቶ አስፈላጊውን አቅጣጫ ይሰጣል፤

3/ በስሩ የተለያዩ ንዑሳን ኮሚቴዎችን በክልል ደረጃ፣ በዞን፣ በወረዳና በቀበሌ ደረጃ ያቋቁማል፣ አስፈላጊውን መረጃ፣ ማስረጃና የስራ ስምሪት ይሰጣል፣ ሪፖርታቸውን ይገመግማል፣ አቅጣጫ ያስቀምጣል፡፡

**15. የክልላዊ ኮሚቴው የአሰራር ስርአት**

1/ የሰላምና ደህንነት ጉዳዮች ቢሮ ወይም አቻ ተቋም የኮሚቴው ሴክሬታሪያት በመሆን ያገለግላል፣

2/ የኮሚቴው አባላት በየእለቱ የመረጃ ልውውጥ የሚያደርጉ ሲሆን በየሶስት ቀኑ የጋራ ስብሰባ ያደርጋሉ

3/ ኮሚቴው ዝርዝር የአሰራር ስርአቱንና በፌዴራል ደረጃ ከተቋቋመው የሚኒስትሮች ኮሚቴ ጋር ተቀናጅቶ የሚሰራበትና የእለት ከእለት ስራውን የሚመበትን ዝርዝር እቅድ ያወጣል፣ ፡፡

4/ በየደረጃው የሚቋቋሙ ንዑሳን ኮሚቴዎች የሚኖራቸውን የስራ ግንኙነትና ሪፖርት ስርአት በተመለከተ ኮሚቴው በሚያወጣው እቅድ መሰረት ይመራል፡፡

**16. የሚኒስትሮች ኮሚቴ እና ክልላዊ ኮሚቴ የስራ ግንኙነት**

1/ የሚኒስትሮች ኮሚቴ እና ክልላዊ ኮሚቴ ቫይረሱን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠርና የሚያስከትሉውን ጉዳት ለመቀነስ የሚሰራ ስራ፣ የወጣው አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያና ሌሎች አቅጣጫዎች በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች ወጥና ተመሳሳይ በሆነ መንገድ እንዲፈጸሙ የሚኒስትሮች ኮሚቴ እቅድ አውጥቶ ወደ ታች ያወርዳል፣ ክልሎችም ከሚኒስትሮች ኮሚቴ የወረደውን እቅድ መነሻ በማድረግ እቅዳቸውን ያወጣሉ፤

2/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ አፈፃፀም መሰረታዊ ጉዳዮችን ሳይለቅ በክልሎች ነባራዊ ሁኔታ በመነሳት በተለየ መልኩ ሊፈጸም የሚችልበትን ሁኔታ በእቅዳቸው ሊወስኑ ይችላሉ፤

3/ ኮሚቴዎቹ በየእለቱ መረጃዎችን የሚለዋወጡ ሲሆን በየሶስት ቀናቱ የጋራ ስብሰባ ያደርጋሉ፤

4/ በሁለቱም ኮሚቴዎች ስር የሚቋቋሙ ንዑሳን ኮሚቴዎች የሚኖራቸውን ግንኙነት በተመለከተ ኮሚቴዎቹ በሚያወጡት የጋራ እቅድ ይወስናሉ፤

## ክፍል ሶስት

## የሐይማኖታዊ፣ የሞት፣የቀብርና ለቅሶ፣የእርድ፣ የበአል፣ የልደትና የግብይት ስርአት፣ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አተገባበርና የአሳንሰር አጠቃቀምን በተመለከተ

**17. የሐይማኖታዊ ስርአት አተገባበርን በተመለከተ**

1/ የሀይማኖት ተቋማት በሀይማኖት ተቋማቱ ውስጥ ሀይማኖታዊ ስርአቱን የሚያከናዉኑ ቁጥራቸው ከአስራ ሁለት ያልበለጠ ሰዎችን ይመድባሉ፤

Scanned by CamScanner

2/ ሀይማኖታዊ ስርአቱን የሚያከናውኑ ሰዎች መቀያየር የማይችሉ ሲሆን፣ ከሀይማኖታዊ ተቋማቱ ውስጥ እንዳይወጡ የምግብና ሌሎች አስፈላጊ ግብአቶችን የሀይማኖት ተቋማቱ የማሟላት ሀላፊነት አለባቸው፤

3/ የማንኛውም ሀይማኖታዊ ስርአት የሚፈፅሙ ሰዎች ሀይማኖታዊ ስርአቱን በሚፈፅሙበት ወቅትም ሆነ በሀይማኖታዊ ተቋማቱ ውስጥ በሚኖሩበት ወቅት ከሁለት የአዋቂ እርምጃዎች በታች ተጠጋግቶ ስርአቱን መፈጸም የተከለከለ ነው፣

4/ በየትኛውም ሀይማኖታዊ ተቋም ሀይማኖታዊ ስርአቱን ከሚያስፈፅሙ ሰዎች ወጪ ሀይማኖታዊ ስርአትን ለመታደምም ሆነ ሌሎች ምክንያቶች በሀይማኖት ተቋማት ግቢም ሆነ ተቋማቱ ውስጥ መግባት የተከለከለ ነው፤

5/ የየትኛውም ሀይማኖት ተከታዮች የሀማኖታቸውን ስርአት በቤታቸው ሆነው መከታተል አለባቸው፣

6/ የየትኛውም ሀይማኖታዊ ተቋም የሀይማኖቱ ተከታዮች ሀይማኖታዊ ስርአቶችን በቤታቸው ሆነው ተግባራዊ ማድረግ እንዲችሉ በቴሌቪዥንና ሬድዮ ጣቢያዎች እንዲተላለፉ ማድረግ ሀላፊነት አለባቸው፣

7/ የሚኒስትሮች ኮሚቴ ከቴሌቪዥንና ሬድዮ ጣቢያዎች ጋር በመነጋገር ሀይማኖታዊ ስርአቶች በቴሌቪዥንና ሬድዮ ጣቢያዎች እንዲተላለፉ የማመቻቸት ሀላፊነት አለበት፣

**18. ከኮቪድ-19 ጋር ባልተገናኘ ሁኔታ ለሚከሰት ሞት የሚኖር የቀብር እና የለቅሶ ስርአትን በተመለከተ**

1/ ማንኛውም ከቀብር በፊት ፣በቀብር ጊዜ እና ከቀብር በኋላ ያለ ስርአት ለሶስት ቀናት ብቻ የሚከናወን ሆኖ ሁለት የአዋቂ እርምጃን በመራራቅ፣ የአፍ መሸፈኛ ማስክ በማድረግ እና ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግ መፈጸም አለበት::

2/ ስርአተ ቀብር ለማካሄድ ከቤት እስከ ስርአተ ቀብር ማስፈጸሚያ ቦታ የሚደረግ የአስከሬን መሸኘት ስርአት በእግር የሚደረግ ጉዞ እና ስርአተ ቀብር በሚከናወነወበት ጊዜ በቀብሩ ቦታ የስርአተ ቀብሩን የሚያከናውኑትን እና የሀዘንተኛውን ቤተሰብ አባላትን ጨምሮ ከ50 በላይ ሆኖ ስርአቱን ማካሄድ የተከለከለ ነው::

3/ ከቀብር በኋላ ለቅሶ መቀመጥ በድንኳን፣ በቤት ውስጥ ወይም ለዚሁ በተዘጋጀ ቦታ ላይ ሲደረግ ሀዘንተኛው እና የቤተሰቡ አባላት እና ለቅሶ የሚደርሰው ሰው ሁለት የአዋቂ እርምጃ ርቀትን በመጠበቅ፣ የአፍ መሸፈኛ ማስክ በማድረግ እና ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግ መከናወን አለበት::

4/ በድንኳን፣ በቤት ውስጥ ወይም ለለቅሶ በተዘጋጀው ቦታ የተቀመጠ ሀዘንተኛ ፣ ቤተሰቡ እና ለቅሶ የሚደርሰው ሰው ሁለት የአዋቂ እርምጃ ርቀት የመጠበቅ፣ የፊትና የአፍንጫ መሸፈኛ ማድረግና በማናቸውም ምክንያት ከሌሎች ሰዎች ጋር ያለመነካካት ግዴታ አለበት::

5/ በለቅሶ እና በቀብር ስርአት ወቅት ከሌሎች ሰዎች ጋር በመነካካት ወይም ሊያነካካ በሚችል መልኩ መመገብ፣ ወይም በለሌሎች ሰዎች በተነካኩና ባልታጠቡ እቃዎች መመገብ የተከለከለ ነው ፤

6/ ሌሎች ከሀይማኖታዊ ተቋማት ውጪ የሚከናወኑ የሀዘን ስርአቶች እንደ ሰባት፣ አርባ ፣ሙት አመትና ሰደቃ የመሳሰሉትን ለማከበር አራትና ከዚያ በላይ ሆኖ መገኘት የተከለከለ ነው::

Scanned by CamScanner

7/ በዚህ አንቀጽ የተቀመጡትን የተከለከሉ ተግባራት ለቅሶው የሚመለከተው እድር ሀላፊ ወይም የሚመከለው አባል ወይም በአካባቢው የሚገኝ ፖሊስ ወይም ሚኒሻ ተቋም በአግባቡ የማስፈጸም የመከታተል እና የመቆጣጠር ግዴታ አለበት፡፡

8/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 7 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ እድር የሌለው ሀዘንተኛ በአካባቢው ለሚገኝ የፖሊስ ወይም የሚኒሻ ተቋም ማመልከት አለበት፤በአካባቢው የሚገኝ የፖሊስ ወይም ሚኒሻ ተቋም የቀብር እና የለቅሶ ስርአቱን በአግባቡ መፈጸሙን የሚከታተል እና የሚቆጣጠር አባል መመደብ አለበት፡፡

9/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 7 እና 8 የተመለከቱት አካላት ሀላፊነታቸውን ካልተወጡ በህግ አግባብ ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

## 19. ከኮቪድ-19 ጋር በተያያዘ ለሚከሰት ሞት የአስከሬን አያያዝና የቀብር ሰነ-ስርዓት አፈፃፀም

### 1. ስለ ቀብር ስፍራ እና ወጪ

ሀ. ማንኛውም ከኮቪድ-19 ጋር በተያያዘ የሚከሰት ሞት በመንግስት በተዘጋጀ የቀብር ቦታ ላይ ብቻ የሚፈፀም ሲሆን ሁሉንም ሀይማኖቶች ያማከለ የቀብር ስፍራ በየክልሉ እና ከተማ መስተዳደሩ የሚዘጋጅ ይሆናል፤

ለ. የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ለዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1/ሀ/ አፈፃፀም ዝርዝር ማንዋል ያዘጋጃል፣

ሐ. መንግስት የቀብር ስነ-ሥርዓቱን የሚያስተባብር እና የሚመራዉ ሲሆን ሙሉ የቀብር ወጭውም በመንግስት ይሸፈናል፤

መ. ከኮቪድ-19 ጋር በተያያዘ በየትኛውም ቦታ ለሚከሰት ሞት አስከሬኑ በመንግስት በተዘጋጀ የትራንስፖርት አገልግሎት ብቻ የሚጓጓዝ ይሆናል፤

ሠ. ከጤና ተቋማት ውጭ የሚከሰቱ ሞቶች በጤና ባለሙያ በሚወሰነው መሰረት ከኮቪድ-19 ጋር የተያያዘ መሆኑ ከተረጋገጠ ለዚሁ በተዘጋጀ ቦታ ቀብሩ ይፈፀማል፡፡

### 2. ስለ ሟች ቤተሰቦች መብትና ግዴታ

ሀ. በቀብር ስነ-ሥርዓቱ ላይ ከቅርብ የቤተሰብ አባላት በስተቀር መሳተፍ አይቻልም፤

ለ. የሟች ቤተሰብ ምንም ዓይነት ንክኪ ሳያደርግ ቀድሞ ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ አስከሬን የማየትና የመሰናበት መብት አለው፤

ሐ. የሟች ቤተሰብ የሞት ማረጋገጫ ሰርትፍኬት የማገኘት መብት አለዉ፤

ሠ. ከቀብር ስነ-ስርዓት በኋላ የሚካሄዱ የለቅሶ መቀመጥ፣ ታዚያ መድረስ ወይም የሟች ቤተሰብን ማፅናናት ተግባራት በዚህ መመሪያ በተመለከተው አግባብ ይፈፀማል፡፡

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Federal Attorney General

Scanned by CamScanner

**3. ስለ አስከሬን አያያዝ**

**ሀ.** በቀብር ስነ-ስርዓት ወቅት የሚደረጉ ማናቸውም ሀይማኖታዊና ባህላዊ ኩነቶች ቫይረሱን የማያስተላልፉ መሆናቸው ሲረጋገጥ ብቻ ይካሄዳሉ፤

**ለ.** በጤና ተቋማት እንዲሁም ከመኖሪያ ቤት ውጭ በሆኑ በተለያዩ ቦታዎች ከኮርና ጋር የተያያዘ ሞት በሚኖርበት ጊዜ አስከሬኑ ወደ ሟች ቤተሰብ ቤት ሳይመጣ የቀብር ስነ-ስርዓቱ የሚፈፀም ይሆናል፤

**ሐ.** የተለየ ውሳኔ ከሌለ በስተቀር ከሟች ቤተሰብ ጋር በመነጋገር በ 24 ሰዓት ውስጥ የቀብር ስነ-ስርዓቱ ይፈፀማል፣

**መ.** በኮረና ምክንያት ከሀገር ዉጭ የሞተን ሰዉ አስከሬን ወደ ሀገር ዉስጥ ማስገባት የተከለከለ ነዉ፤

**ሠ.** ከኮሮና ውጪ ለሚከሰቱ ሞቶች እንደ አስፈላጊነቱ የአስከሬን ምርመራ እየተደረገ ተጋላጭነትን በሚያስወግድ ሁኔታ የሚካሄድ ይሆናል፡፡

**4. ብሔራዊ የቀብር ሥነ ሥርዓት አስተባባሪ ኮሚቴ ስለማቋቋም**

**ሀ.** ብሔራዊ የቀብር ሥነ ስርዓት አስተባባሪ ኮሚቴ በዚህ መመሪያ ተቋሙሟል፤

**ለ.** አስተባባሪ ኮሚቴው በሰላም ሚኒስቴር ሰብሳቢነትይመራል፤

**ሐ.** የኮሚቴዉ አባላት የስራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ፣ የጤና ሚኒስቴር፣የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፣የኢሚግሬሽንና ወሳኝ ኩነት ኤጀንሲ፣ እንደአግባብነቱ የህግ አስከባሪ አካላት እንዲሁም ሌሎች በሚኒስትሮች ኮሚቴ የሚመረጡ አካላት ይሆናሉ፤

መ. ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በተመሳሳይ ሁኔታ በየደረጃው የቀብር ሥነ ሥርዓት አስተባባሪ ኮሚቴ ማቋቋም አለባቸው፤

ሠ. ለቀብር የሚሆን በጀት መመደቡን የማረጋገጥ ሃላፊነት የብሔራዊ የቀብር ሥነ ሥርዓት አስተባባሪ ኮሚቴ እና በክልል እና ከተማ አስተዳደሮች የሚቋቋሙ የቀብር ሥነ ሥርዓት አስተባባሪ ኮሚቴ ይሆናል፡፡

**5. የሀይማኖት ተቋማትና አባቶች ግዴታ**

**ሀ.** የሀይማኖት አባቶች በቀብር ስነ-ስርዓት ወቅት የሚፈፀመውን ፀሎት/ ዱአ/ ፍትሃት በዚህ መመሪያ በተቀመጠው ዝርዝር አፈፃፀም ብቻ ይተገብራሉ፤

**ለ.** የሀይማኖት አባቶች፣ የሟች በተሰብ፣ ጎረቤቶችና መላው ማህበረሰብ ከጤና ተቋማት ውጪ የሚከሰት ሞት ከኮሮና ጋር ተያያዥነት ያለው መሆኑን ከተጠራጠሩ አስከሬን ግነዛና የቀብር ስነ-ስርዓት ከመፈፀሙ በፊት ለሚመለከተው የመንግስት ተቋም የማሳወቅ ግደታ አለባቸው፡፡

**6. የስራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ተግባርና ኃላፊነት**

**ሀ.** የሟች ቤተሰብ የስነ-ልቦና ድጋፍ እና ምክር አገልግሎት እንዲያገኙ ያስተባብራል፤

Scanned by CamScanner

ለ. የተጎጂ ቤተሰቦች በዘላቂነት እንዲቋቋሙ ይሰራል፤

7. የሠላም ሚኒስቴር፣የፖሊስና የፀጥታ ሀይል ተግባርና ኃላፊት

ሀ. ሞት በሚከሰትበት፣ አስከሬን በሚጓጓዝበት፣ የቀብር ስነ-ስርዓት በሚፈፀምበት ወቅት ፀጥታን የማስከበር ስራ ይሰራሉ፤

ለ. ለስራዉ አስፈላጊ የሆነ በጀት ይመድባሉ፤

ሐ. የቀብር ስነ-ስርዓት በሚፈፀምበት ወቅት ማህበራዊ እርቀትን የማስጠበቅ ሥራ እና መሳተፍ ያለበት ሰው ብዛት በህግ በተወሰነው መሠረት መሆኑን ይቆጣጠራሉ፤

መ. ከአስከሬን ዝውውርና የቀብር ስነ-ስርዓት ጋር ተያይዞ የሚከሰቱ ወንጀሎችን ይከላከላሉ፤

ሠ. ከጤና ተቋማት ውጪ የሚከሰት የሞት ጥቆማን ይቀበላሉ፤

ረ. የአስከሬን አያያዝ፣ ትራንስፖረት እና የቀብር ስነ-ስርዓት ላይ መደረግ ስላለባቸው ጥንቃቄዎች የማህብረሰብ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ይሰጣሉ፤

ሰ. የመከላከያ ሚኒስቴር እንደአስፈላጊነቱ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

8. የጤና ሚኒስቴር ተግባርና ኃላፊነት

ሀ. በጤና ተቋማትና ከጤና ተቋማት ውጪ የሚከሰት ከኮሮና ጋር ተያያዥነት ያለው ሞት አስከሬን ይገነዛል፤

ለ. ሙያዊ ስነ-ምግባርን በጠበቀ ሁኔታ በጤና ተቋማት የሚከሰቱ ሞትን ለሟች ቤተሰብ ያረዳል፤

ሐ. የአስከሬን ማሸጊያ ፕላሲትክ ያዘጋጃል፤

መ. የአስከሬን አድርቆ ማቆየት ሲያስፈልግ አስከሬን አድርቆ ያቆያል፤

ሠ. የሞት ማረጋገጫ ሰርትፊኬት ይሰጣል፤

ረ. የአስከሬን አያያዝ፣ ትራንስፖረት እና የቀብር ስነ-ስርዓት ላይ መደረግ ስላለባቸው ጥንቃቄዎች የማህብረሰብ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ይሰጣል፤

ሰ. አስከሬን ለመገነዝ፣ አስከሬን ለማጓጓዝና የቀብር ስነ-ስርዓት ለመፈፀም የሚውል የአደጋ መከላከያ ቁሳቁሶችን ያቀርባል፤

ሸ. ለቀብር አስፈፃሚ ሠራተኞች አስፈላጊዉን ስልጠና ይሰጣል፡፡

9. የኢሚግሬሽንና ወሳኝ ኩነት ኤጀንሲ ኃላፊነት

ሀ. በመላው ሀገሪቱ በኮሮና ምክንያት በጤና ተቋማትና ከጤና ተቋማት ውጪ የሚከሰቱ ሞቶችን ይመዘግባል ፤መረጃ ያደራጃል፤

ለ. በኮሮናና ተያያዥ ጉዳዮች በሚከሰቱ ሞቶች ምክንያት የውርስና የመሳሰሉ ጋር ተያይዞ ለሚከሰቱ ማህበራዊ ቀውስ ለመከላከል የሚረዳ መረጃ ያደራጃል፡፡

The Federal Democratic Republic ... Federal Attorney General

Scanned by CamScanner

**10.በየክልሉና ከተማ አስተዳደር የሚገኙ መዘጋጃ ቤቶች፣ የወረዳዎችና ቀበሌዎች መዋቅሮች ተግባርና ኃላፊነት**

**ሀ.** ለሁሉም ሀይማኖቶች የቀብር ቦታዎችን ያዘጋጃል፤

**ለ.** ለቀብር ስነ-ስርዓት የሚውል በጀት ይመድባል፣

**ሐ.** የአስከሬን አያያዝ፣ ትራንስፖረት እና የቀብር ስነ-ስርዓት ላይ መደረግ ስላለባቸው ጥንቃቄዎች የማህብረሰብ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ይሰጣል፤

**መ.** የሀይማት ተቋማትና እንደ ኢድሮች ያሉ የማህበረሰብ መረዳጃና በጎ አድራጎት አደረጃጀቶችን በማስተባር የሟች ቤተሰቦች የስነ-ልቦና ድጋፍ እና ምክር አገልግሎት እንዲያገኙ ያስተባብራል፤

**ሠ.** በማህበረሰብ ውስጥ የሚከሰት ከኮሮና ጋር የተያያዘ ሞትን ቅኝት ያደርጋል፣ በዚህ መመሪያ መሰረት የቀብር ስነ-ስርዓት እንዲፈፀም ያደርጋል፡፡

**11.የትራንስፖርት ሚኒስቴር ተግባርና ኃላፊነት**

**ሀ.** አስፈላጊዉን የትራንስፖርት አገልግሎት ያቀርባል፤

**ለ.** የትራንስፖረትና ሎጅስቲክ አገልግሎት ያቀርባል፡፡

**12.የገጠር ቀበሌዎች ተግባርና ኃላፊነት**

**ሀ.** በገጠር ቀበሌዎች የቀበሌዉ አስተዳደር የቀብር ስነ-ሥርዓቱን ይመራል፡፡

**ለ.** የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ለቀብሩ ተገቢዉን ሙያዊ ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡

**20. የእርድ ስርአትን በተመለከተ**

1/ ማንኛውንም እርድ ከተፈቀደው የእርድ ቦታ ውጪ ማከናወን የተከለከለ ነው፤

2/ ለማንኛውም አገልግሎት የተፈለገ እርድ በቄራ ብቻ መከናውን አለበት፤

3/ በቄራ መከናወን የማይችል ለቤተሰብ ፍጆታ ብቻ የሚውል እርድን በቤት ውስጥ አራጁ የአፍ መሸፈኛ በማድረግ ማረድ፤ እጅን በውሀ እና በሳሙና በተገቢው መታጠብ እና ለምግብነት የማይውሉ የእንስሳውን አካል በተገቢው ጥንቃቄ ማስወገድ አለበት፤

4/ በቄራ የተከናወነውን እርድ ለመጠቀም በሚወሰድበት ጊዜ እና ጥቅም ላይ በሚውልበት ጊዜ ተገቢውን ጥንቃቄ መደረግ አለበት፤

5/ የቅርጫ ስጋን ለመከፋፈል የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ክፍፍሉን እርዱ በተከናወነበት ቄራ ማደረግ አለበት፤

6/ የእንስሳት እርድን የሚያከናውኑ ቄራዎች የቅርጫ ስጋ ክፍፍል የሚደረግበትን ተገቢ ቦታ እና ክፍፍል የሚያደርግ ሰራተኛ የመመደብ ግዴታ አለባቸው፡፡

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Federal Attorney General

Scanned by CamScanner

**21. የበአልና የልደት ዝግጅቶችን በተመለከተ**

1/ ለበአል እና ለልደት በቤት ውስጥም ሆነ በሌላ ቦታ የሚደረጉ ዝግጅቶች የቤተሰብ አባላት ከሆኑ ውጪ ያሉ ሰዎች ጋር ተጠራርቶ ማክበር የተከለከለ ነው፤

2/ ለዚህ አንቀጽ ተፈጻሚነት ቤተሰብ ማለት በአንድ ቤት ውስጥ በአንድ ላይ የሚኖሩት አባላት ማለት ነው፤

3/ በማንኛውም የሀዘን እና የደስታ ዝግጅቶች ላይ እያንዳንዱ ሰው ለብቻው በተዘጋጀለት መመገቢያ እና መጠጫ መጠቀም አለበት፤ እርስ በእርስ መጎራረስ እና በጋራ እቃ ከቀረበ ማእድ መመገብ የተከለከለ ነው፤

**22. የግብይት ስርአትን በተመለከተ**

1/ ማንኛውም ለግብይትም ሆነ ለሌላ አላማ በገበያ ቦታዎች፣ በንግድ እቃ ማከፋፈያዎች፣ በሱቆች፣ ዳቦ ቤቶች ወይም በማንኛውም ግብይት በሚፈፀምበት ቦታ የሚሄድ ሰው ከሻጭ፣ ከገዥ ወይም በቦታው ከሚገኝ ማንኛውም ሰው ከሁለት ሜትር ወይም ከሁለት የአዋቂ ሰው እርምጃ በታች በሆነ ርቀት ላይ ሆኖ ማውራት፣እቃ መቀባበል፣ መሸጥ፣ መግዛት፣ መቆምም ሆነ መቀመጥ የለበትም፤

2/ በሚመለከተው አካል ለገበያ ቦታነት ባልተከለሉ. ከሚታወቁና ከተፈቀዱ ገበያዎችና የግብይት ቦታዎች በስተቀር በመንገድ ዳር፣ በጎዳና ላይ ወይም በማንኛውም ቦታ ላይ መገበያየት የተከለከለ ነው፤

3/ የየአካባቢው መስተዳደሮች ማህበረሰቡ ከአካባቢው ሳይርቅ፣ ሳይጠጋጋና ሳይጨናነቅ መገበያየት እንዲችል ከነበሩትና ከሚታወቁት የገበያ ቦታዎች ተጨማሪ በርካታ ገበያዎችን የማቋቋም ወይም የማዘጋጀት ሀላፊነት አለባቸው፤

4/ ማንኛውም በገበያ ቦታዎች፣ በንግድ እቃ ማከፋፈያዎች፣ በሱቆች፣ በጉሊት የግብይት ቦታዎች ወይም በማንኛውም ግብይት በሚከናወንበት ቦታ የሚገኝ ሰው በአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ማስክ ወይም በማንኛውም የኮቪድ-19 ቫይረስ ወደ አፍና አፍንጫ እንዳይገባ ሊከላከል በሚችል ልብስ አፍና አፍንጫውን የመሸፈን ግዴታ አለበት፤

5/ በገበያ ቦታዎች በሻጭና በገዥ መካከል ሊኖር የሚገባውን የሁለት የአዋቂ እርምጃዎች አካላዊ ርቀት የአካባቢው መስተዳድር ወይም የሚመለከተው የመንግስት አካል ለከቶ በግልጽ በሚታይ ሁኔታ ምልክት የማድረግ ሀላፊነት አለበት፤

6/ ማንኛውም በንግድ መደብር፣ ሱቅ፣ ማከፋፈያ ወይም የንግድ ቤት ውስጥ የንግድ ስራ የሚሰራ ሰው በእርሱና በገዥው መካከል ሊኖር የሚገባውን የአዋቂ እርምጃ አካላዊ ርቀት የሚያሳይ ግልጽ ምልክት ቀድሞ ማስቀመጥ አለበት፤

7/ የፌዴራል መንግስት እና የክልል መንግስታት ህብረተሰቡ ከአካባቢው ሳይርቅ የሚያስፈልጉትን የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርቶች በተመጣጣኝ ዋጋ በቀላሉ ማግኘት እንዲችል የሸማች ማህበራትን፣ የህብረት ስራ ድርጅቶችን፣ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን እና ሌሎች አስፈላጊ አደረጃጀቶችን እንዲጠናከሩና በተገቢው ሁኔታ እንዲሰሩ የማድረግ ግዴታ አለበት፤

Scanned by CamScanner

8/ በየደረጃው የሚገኙ የሸማች ማህበራት፣ የህብረት ስራ ድርጅቶች እና ሌሎች አደረጃጀቶች ለህብረተሰቡ የሚያስፈልጉ የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርቶችን በየአቅራቢያው በማቅረብ በተመጣጣኝ ዋጋ ለህብረተሰቡ ያለአድሎ የማዳረስ ስራ መስራት አለባቸው፤

9/ በማንኛውም የግብይት ቦታ የሚገኝ ሻጭ ከገዥ ጋር የሚያደርገውን ንክኪ ለመቀነስ እንዲያስችለው ገዥው ለገዛው እቃ የሚከፍለውን ገንዘብ የሚያስቀምጥበት እቃ የማዘጋጀትና የተሸጠውንም እቃ ገዥው አንስቶ እንዲወስድ የማድረግ፣ ወይም እቃውን አንስቶ መስጠት ግዴታ በሚሆንበት ጊዜ የእጅ ጓንትን በመጠቀም የመስጠት፣ እንዲሁም በእጅ በመንካት ታይተው የሚገዙ የንግድ እቃዎችና የእንስሳት ግብይቶች በተመለከተ ገዥው የሚጠይቀውን ወይም የሚገዛውን እቃ ወይም እንስሳ ለመንካት የእጅ ጓንት የመጠቀም ግዴታ አለበት፤

10/ ማንኛውም የኢንተርኔት ወይም አንላይን ግብይት የፈፀመ ድርጅት ወይም ነጋዴ ግብይት የተፈፀመትን እቃ ለገዥው በአድራሻው በመውሰድ የማስረከብ ግዴታ አለበት፤

11/የመንግስት ተቋማት ደንበኞቻቸው በአካል ሳይገኙ በኤሌክትሮኒክ መንገድ አገልግሎት ማቅረብ እና ማግኘት የሚያስችሉ በመንግስት /በቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ሚኒስቴር/ የተዘጋጁ እና የተረጋገጡ ስርዐቶች የመጠቀም ግዴታ አለበት ፡፡

**23. የአሰሪ ሀላፊነትን በተመለከተ**

ማንኛውም አሰሪ፡-

1/ ሰራተኞቹና ተገልጋዮች በስራ ቦታ ራሳቸውን ከኮቪድ-19 ለመከላከል እንዲያስችላቸው ሊጠቀሙበት የሚገባ የውሃ፣ ሳሙና እና ሌሎች አስፈላጊ የንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁሶችን በበቂ ሁኔታ በነፃ የማቅረብና በአግባቡ እንዲጠቀሙበት ግንዛቤ የመፍጠር ግዴታ አለበት፤

2/ ሰራተኞቹ በስራ ቦታ ራሳቸውን ከኮቪድ-19 ለመከላከል እንዲያስችላቸው ሊጠቀሙበት የሚገባ የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ማስክ የማቅረብና ስለአጠቃቀሙም ለሰራተኞቹ ግንዛቤ የማስጨበጥ ግዴታ አለበት፤

3/ ሰራተኞቹና ተገልጋዮች ተቀራርበው እንዳይሰሩ፣ እንዳይቀመጡና የተቀራረበ አገልግሎት የመስጠትና አገልግሎት የመቀበል ተግባር እንዳይኖር በሰራተኞች መካከል እና በሰራተኛና በተገልጋይ መካከል ቢያንስ የሁለት ሜትር ርቀት ተጠብቆ እንዲከወን ርቀቱን ለኩቶ ተገቢውን ምልከት የማድረግና ተግባራዊ እንዲደረግ ግንዛቤ የመፍጠር ኃላፊነት አለበት፤

4/ ሰራተኞቹን ከመኖሪያ አካባቢያቸው ወደ ስራ ቦታ እና ከስራ ቦታ ወደ መኖሪያ አካባቢያቸው የሚያደርስ ተሽከርካሪ ሰርቪስ የመመደብና ተሽከርካሪውም በእያንዳንዱ ጉዞ ተሽከርካሪው ካለው የወንበር ብዛት ከግማሽ በላይ እንዳይጭን እና መስኮቶችም ከፍት እንዲደረጉ ለተሽከርካሪው ሾፌር ተገቢውን ትዕዛዝ የመስጠትና የመከታተል ኃላፊነት አለበት፤

5/ በስራ ቦታ ግቢ ወይም አካባቢ ስለ ኮቪድ-19 ምንነት፣ የመተላለፊያ መንገዶች እና መከላከያ ስልቶች ግንዛቤ የሚያስጨብጡ ፖስተሮችን፣ ስዕሎችን፣ ጽሁፎችንና ሌሎች ማሳያዎችን ለሰራተኞች በሚገባቸው ቋንቋ በግልጽ ቦታ ላይ የመለጠፍ ግዴታ አለበት፤

Scanned by CamScanner

6/ ከሰራተኞች ጋር የሚያደርጋቸውን ስብሰባዎች የማስቀረትና የስራ መመሪያዎችን በተቻለ መጠን በኢሜልና በሌሎች የኤሌክትሮኒክ መገናኛ ዘዴዎች ማስተላለፍ አለበት፤

7/ የካፍቴሪያ አገልግሎት የሚሰጥ ከሆነ የካፊቴሪያ የአገልግሎት ጊዜን በማራዘም ሰራተኞች ተጠጋግተው ንዳይጠቀሙ ግንዛቤ የማስገንዘብና የመጠቀሚያ ጠረጴዛዎችም ቢያንስ በየሁለት ሜትር ርቀት ላይ እንዲቀመጡ የማስደረግ ኃላፊነት አለበት፤

8/ ሰራተኛው የስራ መገልገያ ቁሳቁሱን የሚያስቀምጥበት የግል ማስቀመጫ የማዘጋጀት ግዴታ አለበት፤

9/ ሰራተኞች የስራ የደንብ ልብስ የመልበስ ግዴታ ያለባቸው ከሆነ የሚለብሱት የደንብ ልብስ ንጽህናው የተጠበቀ፣ በፀረ-ተህዋስ ማጽጃ የፀዳና በየግል ማስቀመጫቸው የሚቀመጡ የደንብ ልብሶችን እንዲለብሱ የማድረግ፣ ግንዛቤ የመፍጠርና የመከታተል ኃላፊነት አለበት፤

10/ የጋራ መገልገያ ቁሳቁሶች በጽዳት ሰራተኞች አማካኝነት ቶሎ ቶሎ በፀረ-ተህዋስ ማጽጃ እንዲፀዱ የማስደረግ ኃላፊነት አለበት፤

11/ የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከሚያስቀምጠው ስርዓት ውጭ ወይም ሚኒስቴሩ ሳያውቀውና ሳይፈቅድ የሰራተኛን የስራ ውል በማንኛውም ሁኔታ ማቋረጥ፣ ደሞዝ ማገድ፣ ደሞዝ መቀነስ እና መከልከል የለበትም፤

12/ የኮቪድ-19 ምልክት በግልጽ የታየባቸውን ወይም ምልከቱ ታይቶባቸዋል ተብለው የሚጠረጠሩ የስራ ባልደረቦችን በጊዜያዊነት ለማቆየት የሚችል ጊዚያዊ የማቆያ ስፍራ የማዘጋጀትና ምልከቱ በግልጽ የታየበትን ሰራተኛ በአንድ ሰአት ውስጥ ለሚመለከተው የጤና ተቋም ማሳወቅና መላክ አለበት፤

13/ በድርጅቱ ኃላፊ የሚመራ አምስት አባላት ያሉትና ሁለት የሰራተኞች ማህበር አባላት የሚሳተፉበት ተጠሪነቱ ለሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሆነ በስራ ቦታ የኮቪድ-19ን መከላከልና ቁጥጥር ስራን የሚመራና የሚከታተል የኮቪድ-19 መከላከል ኮሚቴ ማቋቋም አለበት፤

14/ ኮቪድ-19ን ከመከላከልና መቆጣጠር ስራ ጋር በተያያዘ በስራ ቦታ ያለውን እንቅስቃሴና አጠቃላይ የአተገባበር ሂደት ለሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ለሚመለከተው አካል ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

**24. የሰራተኛ ሃላፊነትን በተመለከተ**

ማንኛውም ሰራተኛ፡-

1/ በስራ ቦታ በአሰሪ የሚቀርበውን የንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁስ በአግባቡ በመጠቀም የእጅ ንጽህናን የመጠበቅ ግዴታ አለበት፤

2/ በስራ ቦታ በአሰሪ የሚቀርብለትን የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ማስክ በአግባቡ የመጠቀም ግዴታ አለበት፤

3/ ከሌላ ሰራተኛም ሆነ ከአሰሪ ጋር የእጅ ለእጅ ሰላምታና አካላዊ ንክኪ ማድረግ የለበትም፤

4/ ኮቪድ-19 ን ከመከላከል ጋር በተያያዘ በአሰሪ የሚሰጡ መመሪያወችና የጥንቃቄ እርምጃዎች የመቀበልና በአግባቡ የመተግበር ግዴታ አለበት፤

The Fed...
Democratic Republic o...
Federal Attorney General

Scanned by CamScanner

5/ በስራ ቦታ በሚያስለው ወይም በሚያስነጥሰው ወቅት አፍና አፍንጫውን በሶፍት ወይም በክንዱ የመሸፈን ግዴታ አለበት፤

6/ የስራ መገልገያ ቁሳቁሶችን፣ የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችንና ሌሎች ማናቸውም ቁሳቁስ በተቻለ መጠን በጋራ መጠቀም የለበትም፤

7/ የኮቪድ-19 ምልክት በራሱ ላይ መከሰቱን ወይም በሌላ ሰራተኛ ላይ ምልክቱ ታይቷል ብሎ ካመነ በስልክ ወይም በማንኛውም የኤሌክትሮኒክስ መገናኛ ዘዴ ሁኔታውን ለአሰሪው ወይም ለቅርብ ሀላፊው በቶሎ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፤

8/ ለስራ የሚጠቀምበትን መገልገያ መሳሪያ በንጽህና የመያዝና በግሉ የማስቀመጫ ቦታ ላይ በአግባቡ የማስቀመጥ ግዴታ አለበት፤

**25. የኮቪድ-19 መከላከል ኮሚቴ ተግባርና ግዴታዎች**

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 23 ንዑስ አንጽ (13) መሰረት የሚቋቋመው የኮቪ.-19 መከላከል ኮሚቴ፡-

1/ በስራ ቦታዎች በመንቀሳቀስ ሰራተኞች ኮቪድ-19ን ለመከላከል የሚያስችሏቸውና የሚያስፈልጓቸው ኬሚካሎችና ቁሳቁሶች በአሰሪዎቻቸው የተሟሉላቸው መሆኑን የማረጋገጥና በአጠቃላይ አሰሪዎች በዚህ መመሪያ አንቀጽ 23 መሰረት የተጣሉባቸውን ግዴታዎች በአግባቡ እየተወጡ መሆኑን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፤

2/ በስራ ቦታዎች በመንቀሳቀስ ለኮቪድ-19 የሚያጋልጡ ሁኔታዎችን የመከታተል፣ የመለየት እና የማስተከያ እርምጃ የመውሰድና የማስወሰድ ኃላፊነት አለበት፤

3/ በስራ ቦታዎች በመንቀሳቀስ ሰራተኞች ተገቢውን የንጽህና መጠበቂያና መከላከያ ቁሳቁስ በአግባቡ እየተጠቀሙ ስለመሆኑ የማጣራት፣ የማረጋገጥ፣ የመከታተልና የአጠቃቀም ችግሮችን ከስራ ኃላፊዎች ጋር በመነጋገር እንዲስተካከሉ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፤

4/ የኮቪድ-19 ምልክት የታበትን ሰራተኛ ወይም በቫይረሱ ተይዟል ተብሎ የሚጠረጠር ሰራተኛ ከአሰሪ ድርጅቱ ጋር በመነጋገርና ሌሎች ሰራተኞችን ለቫይረሱ በማያጋልጥ ሁኔታ ተገቢውን ድጋፍ በማድረግ ሰራተኛው ወደሚመለከተው የጤና ተቋም የሚሄድበትን ሁኔታ የማመቻቸት፤ እንዲሁም ከሰራተኛው ጋር ንክኪ የነበራቸውን ሌሎች ሰራተኞች ከሚመለከተው የጤና ተቋም ጋር በመሆን የማጣራትና የመለየት ኃላፊነት አለበት፤

5/ የሰራተኞች የስራ ቦታ ያለውን የጽዳት ሁኔታ፣ የአሰራርና አጠቃቀም ስርዓት እና አጠቃላይ የስራ ቦታው ለኮቪድ-19 ያለውን ተጋላጭነት የመገምገም፤ ተጋላጭ ሆኖ ሲገኝም ከአሰሪው ጋር በመነጋገር ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፤

6/ ለአሰሪዎችና ለሰራተኞች በኮቪድ-19 ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስርዓቶችን የማስፋፋት እና ወቅታዊ መረጃዎችን የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Federal Attorney General

Scanned by CamScanner

**26. የአሳንሰር አጠቃቀምን በተመለከተ**

1/ ለማንኛውም ሰው አሳንሰር መጠቀም የተከለከለ ነው፤

2/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው ቢኖርም ህንፃው ረጅም በመሆኑ ወይም ተጠቃሚው የአካል ጉዳተኛ በመሆኑ አሳንሰር መጠቀም የግድ ከሆነ በአንድ አሳንሰር ውስጥ አንድ ሰው ሊጠቀም ይችላል፣

3/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 የተደነገገው ቢኖርም በሌላ አሳማኝ ምክንያት በአንድ አሳንሰር ውስጥ ከአንድ ሰው በላይ መጠቀም የሚያስገድድ ሁኔታ ካጋጠመ ሁለት የአዋቂ ርምጃ ርቀት በመጠበቅና የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ በመጠቀም ሁለት ሰዎች ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡

**ክፍል አራት**

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

**27. የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርአትና በሌሎች የወንጀል ህጎች ላይ የተደነገጉ ስነ-ስርአታዊ ድንጋጌዎች አፈፃጸም**

1/ በደንቡ አንቀፅ 6/1/ መሰረት በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርአት ህጉና ሌሎች አዋጆች ላይ የተመለከቱ የወንጀል ስነ-ስርአት ድንጋጌዎች ተፈጻሚነታቸው የታገደ በመሆኑ ህግ አስከባሪ አካላት በነዚህ ህጎች ላይ የተመለከቱ የጊዜ ገደቦችና ሌሎች ድንጋጌዎችን የማክበር ግዴታ የለባቸውም፣

2/ ተጠርጣሪዎችና ተከሳሾች በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርአት ህጉና በሌሎች የ ወንጀል ህጎች ላይ የተመለከቱ ስነ-ስርአታዊ ድንጋጌዎች ተጥሰዋል በሚል የሚያቀርቧቸው አቤቱታዎች ተቀባይነት አይኖራቸውም፣

3/ በደንቡ አንቀፅ 6/1/ መሰረት በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርአት ህጉና ሌሎች አዋጆች ላይ የተመለከቱ የወንጀል ስነ-ስርአት ድንጋጌዎች ተፈጻሚነታቸው የታገደ በመሆኑ የህግ አስከባሪ አካላት ከአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ጋር የተያያዙም ሆነ ግንኙነት የሌላቸው ወንጀሎች በሚፈጠሩበት ጊዜ የወንጀል ስነ-ስርአታዊ ድንጋጌዎችን መከተል ሳያስፈልጋቸው ስራቸውን ማከናወን ይችላሉ፤

**28. መመሪያውን ስለማሻሻል**

በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ የተፈጻሚነት ዘመን ውስጥ ይህን የአፈጻጸም መመሪያ ለማሻሻል የሚያስፈልጉ ጉዳዮች ከተከሰቱ መመሪያው በሚኒስትሮች ኮሚቴ ሊሻሻል ይችላል፡፡

**29. የተሻሩና ተፈፃሚ የማይሆኑ ሕጎችና አሰራሮች**

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረኑ ማናቸዉም ሕጎችና አሰራሮች በዚህ መመሪያ በተሸፈነ ጉዳይ ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸዉም፡፡

**30. የመተባበር ግዴታ**

ማንኛዉም ሰዉ ለዚህ መመሪያ ተፈፃሚነት መተባበር ግዴታ አለበት፡፡

Scanned by CamScanner


**31. መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ**

1) ይህ የአፈጻጸም መመሪያ በሚኒስትሮች ኮሚቴ ከጸደቀበት ዕለት ጀምሮ የጸና ይሆናል፤

2) የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ከተነሳ የዚህ መመሪያም ተፈጻሚነት አብሮ ያበቃል፡፡

**ሚያዝያ 10 ቀን 2012 ዓ.ም**

**የሚኒስትሮች ኮሚቴ**




Scanned by CamScanner